# የህዝብ መከራ ከጥይት እስከ ኑሮ ውድነት

Teshale WoldeGabriel

እንደሚታወቀው ባሳለፍናቸው ም/ዓመታት በዲያብሎስ ፈረስ ላይ ተፈናጠው ሽቅብ እየጋለቡ የሰው ልጅን የሚያክል ክቡር ፍጡር እንደምናምንቴ ጠፍ እያሳደዱ ፣ እያቃጠሉ ፣ እያረዱ ባላቸው ሀይል ሁሉ የዘር ማጥፋት ህልማቸውን እውን እያደረጉ ዲያብሎስ የተጸናወታቸው አምባገነን መሪዎች ትውልድ የማይሽረውን ጠባሳ ጥለው እንዳለፉና አሁንም መልካቸውን በመቀያየር በተለያየ የአለማችን ክፍል ሀገራት ብቅ ጥልቅ ማለታቸውን የማያስተውል ህሊና አለ ለማለት አያስደፍርም ፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ አምላካችን ክብር ይግባውና በአንጻሩ እነዚህን ከራሳቸው የተጣሉ ደም ያሰከራቸው ጭራቆችን በዝምታ መመልከት ያልቻሉ እራሳቸውን ለሌላው ነጻነትና መኖር መስዋዕት ያደረጉ በርካታ አባቶችን እናቶችን ወንድሞችንና እህቶችን ለማየት አስችሎናል ፡፡ በሰፈሩት . . . እንዲሉም ነውና በአንድ ወቅት የማያልፉ ዘላለማዊ መስለው ቢሰማቸውም ሀይላቸውን ቁጤማ አይናቸውን ጨለማ አድርጎ እንዳሳየን የምንረሳው የሩቅ ትዝታ አይደለም ፡፡

ዲያብሎስ ግን ዛሬም አያንቀላፋም . . . ጥፍሮቹን በማስከተል አይኑን አጎጥጦ ጥርሱን አግጦ የከሸፈ አላማውን ለማሳካት በሚመስል መልኩ ለአሳቻ ጊዜያት በአሳቻ አንደበቱ እየሰበከ የእልቂት መረቡን በሰፊው ዘርግቶ ደፋ ቀና ሲል ይስተዋላል ፡፡ ከነዚህም ውስጥ በፍቅሩ ታውረው በመረቡ ተተብትበው መፍለጥ መቁረጥ ከጀመሩ አስርት አመታትን ካስቆጠሩት ጥቂት የራሳቸውን ጅብደኞች መሀከል የኛዎቹ አምባገነኖች በግንባር ቀደምትነት ይጠቀሳሉ ፡፡ የእኛዎቹ ጉዶች ከበርካታ ጊዜያት በፊት ጀምሮ ሰዎች ሰዎችን በተለያዩ ከባድና ቀላል ሰው ሰራሽ የጦር መሳሪያዎችን በጅምላም ሆነ በተናጠል ሲያጠፉ የነበረና እያጠፉ እንዳለ የሚካድ ሀቅ አይደለም ፡፡ ዛሬ የሚታየው ደግሞ ከዚህ ባልተለየ መልኩ በሚያስገርም ሁኔታ መልካቸውንና ሀሳባቸውን ቀይረው በጭቁኑ የሀገራችን ህዝብ ላይ በተቀነባበረ እርኩስና ግብዝ አላማ የጣሉት የሞት ጥላ ነው፡፡

ይህን ስል መቼም ምን አዲስ ነገር ተፈጠረ ብላችሁ እንደማትጠይቁ እርግጠኛ ነኝ ፡፡ ገና ሚሊንየሙ መጣ መጣ እየተባለ ባለበት ወቅት አጋጣሚውን በመጠቀም በተለያየ መንገድ ዛሬ ያንዱን ነገ ዳግም የሌላኛውን ሸቀጥ ዋጋ ጣራ በማድረስ እና ቅጥ ያጣ

የኢኮኖሚ ዝቅጠት? ህዝቡን እና ሀገሪቱን መበጥበጥ የጀመሩት ፡፡ ይሕውም ከጥቂት ባለሀብቶች ጋር በመመሳጠር እከከኝ ልከክልህ በሚለው ጨዋታቸው የሀገሪቱን ደካማ ኢኮኖሚ በቁጥጥር ስር በማዋል ፣ የተቀረው ሰላም ፣ ፍትህ ፣ እውነት . . . የተጠማ ብዙሃን ህዝብ አንደበት እየተዘጉ የነሱን ኪስ በማድለብ የስልጣን ዘመናቸውን ለማራዘም እየተጠቀሙበት ያለው ዘዴ ከዚህ ከዘር ማጥፋት የተለየ ነው ሊባል አይችልም፡፡

ይነስም ይብዛ መቼም እኛ በስደት ላይ ያለን ሰዎች ሌሎች ሌሎች የህይወት ጥያቄዎቻቸውን ያሳሰቡን እንደሆነ እንጂ እንደሀገራችን በሚሊዮን የሚቆጠር ህዝብ ምን እንብላ የሚለው ጥያቄ አያሳስበንም ፡፡ለዚህም ልዑል አምላክ የተመሰገነ ይሁን ፡፡ ታዲያ በዚህ የዕለት ጉርሱን አንዴ እንኳን አግኝቶ ነፍሱን ለማቆየት ከህይወት ጋር ትንቅንቅ በፈጠረ ምስኪን ህዝብ ላይ እንዲህ ያለ ታይቶና ተሰምቶ የማይታወቅ የዋጋ ንረት ከጤነኛ አዕምሮ የመነጨ ነው ትላላችሁ ?

በወቅቱ ሄደን በአይናችን ለማየት የታደልንም ሆነ እዚህ በውጭ ያለነው በተለያዩ መገናኛ ብዙሃኖች እንደሰማነው ሁሉንም እግዚኦ ብለን አሳልፈናል ፡፡ ዛሬ ግን እየሰማን ያለነው ፍጹም በጆሮ እንግዳ የሆነና የማይታመን ነውና አንድ ልንለው ይገባል ባይ ነኝ ፡፡ ለጊዜው መንገዱ ሁሉ አልጋ በአልጋ የሆነላቸው ቢመስላቸውም የዚህ የደሀ ህዝብ እምባ የት ሊያደርሳቸው እንደሚችል ዞር ብለው መመልከት ቢችሉ ብልህነት ነውና ከወዲሁ ቢያስቡበት እላለሁ ፡፡

እግዜያብሄር ኢትዮጵያን ይባርክ